የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ የትንሳዔ በዓል መልዕክት :

የክርስትና እምነት ተከታይ የሆናችሁ መላ የሀገሬ ሕዝቦች፤ ለሁለት ወራት ያህል በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት እና ከአምላክ ጋርም በተመሰጦ ልቦና በመገናኘት ያሳለፍነውን ዐቢይ ጾም እንኳን በሰላም እና በፍቅር አጠናቀቃችሁ፤ እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው አደረሳችሁ፤ አደረሰን! ከመነሣት የበለጠ ታላቅ ነገር የለምና ትንሳኤ ታላቅ በዓል ነው። በዓሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን ድል አድርጎ፣ ‹መግነዝ ፍቱልኝ፤ መቃብር ክፈቱልኝ› ሳይል መነሣቱን የምናበስርበትና የምናስብበት በዓል ነው። ከአእምሮ በላይ የሆነውን ሥራ ዕውብ ድንቅ ብለን፣ በደስታና በፍቅር የምናከብርበት ታላቅ በዓል ነው፤ ከመሞት በላይ ውርደት ከመነሣትም በላይ ክብር የለምና። ከሞት አጠገብ ሕይወት፣ ከመቃብር አጠገብ ትንሳኤ መኖሩን የምናስብበት፣በአዕምሯችንም ሰሌዳ የምናትምበት በዓል ነው፤ ትንሣኤ።

በትንሳኤ ጉዞ ውስጥ ዓርብ፣ ቅዳሜና እሑድ አሉ። ዓርብ እውነትና ሐሰት፣ወዳጅና ጠላት፣ ተስፋና ሥጋት፣ እምነትና ፍርሃት፣ እምባ እና ሳቅ፣ ብርሃንና ጨለማ፣ ጽናትና ድካም የተቀላቀሉበት ጊዜ ነው። እየነጋ ባለ ፀሐይና በድቅድቅ ጨለማ መካከል ያለውን ቀጭን መሥመር ለመለየት የሚያስቸግርበት ቀን ነው - ዓርብ። በአንድ በኩል በጦር ጉልበታቸው የሚተማመኑ ሮማውያን፣ በሌላ በኩል እናውቃለን የሚሉ የአይሁድ ሊቃውንት አንድ ሆነው ፀሐይ እንዳትወጣ የሚታገሉበት ቀን ነው -ዓርብ። የተስፋ ፀሐይ እንጂ አማናዊት ፀሐይ ገና አልወጣችም። ውስጥ ዐዋቂ ነኝ የሚለውን ይሁዳን ያገኙ ግብዞች፣ ፀሐይን የቀበሩ መስሏቸው፣ ሃውልት ሊያቆሙባት የሚሮጡባት ቀን ነች - ዓርብ።በዕለተ ሆሳዕና ምንጣፍ

ሲያነጥፍና፣ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ ሲደግፍ የነበረው ሕዝብ፣ በዕለተ ዓርብ ‹ሰቀለው ሰቀለው› ይላል።

ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ደም ይለብሳል፤ ከዋክብትም ይረግፋሉ። በዚያ ሰዓት ነገን አሻግሮ ማየት፣ ከእውነትም ጋር አብሮ መቆም ከባድ ነው። ሀገር ‹ሆ› ብሎ ከሚነጉድበት ሰሜት መውጣት፣ የግራ ቀኙን ጩኸት ታግሶ - ዓርብ በሐሳብ፣እሑድ ግን በተግባር ከሚታየው ትንሳኤ ጋር ለመቆም፣ እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ ያለ ጽኑዕ ሰብዕና ይጠይቃል። ሰቀለው ከሚለው የዓርቡ ጩኸት ሣልሰት የትንሳኤ ድል እንደሚኖር ማሰብ፤ ደም ከለበሰችው ጨረቃ ወዲያ አማናዊ ብርሃን እንደሚኖር ለማየት፣ ከሚረግፉት እልፍ አእላፍ ከዋክብት ባንሻገር ሞትን በሞት በሚገድል አምላክ ክንድ የሚረግፉ ችግሮች መኖራቸውን ለማመን ብርቱ ሰው መሆን ይፈልጋል። ዓርብ ዕለት ከበዛው ጩኸት ይልቅ ከተሰቀለው እውነት ጎን ለመቆም ልብ ያለው ሰው መሆን ይጠይቃል። ቅዳሜ ድንግዝግዝ ነው። እውነት ድል የተነሣች፣ ፀሐይም ጨልማ የቀረች ፣ መቃብርም ታትማ የምትኖር፣ ሞትም አንቆ የሚያሰቀር፣ ሲኦልም አሸጋ የምትቀብር የሚመሰልበት ወቅት ነው። አሸናፊና ተሸናፊ አይለይም። እንዲህ ባለው ወቅት እምነት፣ ጽናትና ቆራጥነት እንጂ ማሰረጃና መረጃ ለማቅረብ ከባድ ይሆናል። በመቃብሩ ዙሪያ ጠባቂዎች፣ በመቃብሩም ላይ ማኅተም አለ። ከሁሉ ይሻላሉ የተባሉት ሐዋሪያት ተበትነዋል። ሕዝቡም የምሥራች ወሬውን ጨርሶ - አቋሙም በወሬ ብዛት ተፈረካክሶ የክፋት መልዕከተኞች የክፋት ወሬ በሕዝቡ ውስጥ ተናፍሶ፣ ወሬውም ከብዙዎች ዘንድ ደርሶ...ሥጋትና ተስፋ መቁረጥ አይሏል። ሕዝቡ የሸንፈትና የድካም ነገር ያወራል።ዓርብ ዕለት ያየው ሰቅለት - ደም - ግርፋት - ጩኸት እና እንግልት የመጨረሻው መጨረሻ መስሎት አለቀ፣ ደቀቀ - ይላል።

የትናንቱን የዓርብን ነገር የሚያወሩ ብዙ ናቸው። የነገውን የእሑድን

ምሥጢር ለመተንበይ የቻሉ ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ገብቶናል፣ ተረድተናል፣ ተምረናል፣ አውቀናል የሚሉት እንኳን በወሬው ተሸንፈዋል፤ በስሜቱ ተውጠዋል። ነፋሱንና ጎርፉን መቋቋም አቅቷቸው፣ በነፋሱና በጎርፉ ተወስደዋል። አንድ የማይቀር እውነት ግን አለ። ትንሳኤ ይመጣል። ጩኸት ቢበረታም፣ ሽብር ቢነዛም፣ ኃያላን ቢነሱም፣ እውነት የተሸነፈች ብትመስልም - ትንሳኤ ግን በግድ ይመጣል። ወሬውና ሽብሩ አስደናቂውን ትንሳኤና ትንሳኤውን ተከትሎ የሚመጣውን እልልታ ፈጽሞ ሊያስቀረው አይችልም። ጠባቂዎቹና ማኅተሙ፣ የሞት ፉከራ እና የጉልበተኞች ጉርምርምታ በጭራሽ ትንሣኤን አያግዱትም። የብዙዎች ተስፋ መቁረጥና የተሰናካዮች ወደ ኋላ መመለስ ከመምጣት አይገቱትም። ከሞት አጠገብ ሕይወት፤ ከመቃብርም አጠገብ ትንሳኤ አለ። እምባ እና ደም ያጠየሟት ዓርብ የሥርየትና የሐሴት መሠረት ነች። የጭንቋ ቀን ቅዳሜ የትንሳኤው የመዘጋጃ ቀን ናት። ከዚህ ሁሉ በኋላ በዝማሬ የምትደምቅ እና በትንሳኤም የምትከብር እሑድ መኖሯን ያመነ ሰው - እርሱ እውነትም ወንዝ ተሻጋሪ ሰው ነው። ትንሳኤ የዘገየ ይመስላል እንጂ አይቀርም። አለቀ፣ ደቀቀ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ የሚሉትን ሁሉ አሳፍሮ ክርስቶስ በእኩለ ሌሊት ተነስቷል። መቃብሩ ባዶ ነው። ‹ሞተ› የሚለው መርዶ ቀረ። ዜናው - ተነሳ - ሆነ። አለቀ የሚለው መርዶ ቀረ -ዜናው -እንደገና ተጀመረ - ሆነ። ተስፋ መቁረጥ ታሪክ ሆኖ - ራሱ ተስፋ ከሞት ተነሳ። የተበተኑት ተሰበሰቡ። ፈርተው የሸሹት ተመለሱ። ወሬና ሽብር ያስቀራቸው እንደገና መጡ። የተቆረጠ ተቀጠለ፤ የደከመ በረታ፣ ታሪክ ተለወጠ። ትንሳኤ መኖሩ ብቻ ሳይሆን በምንም ሰበብ - በማንም ክልከላ-በየትኞቹም የመቃብር ጠባቂዎች ብርታት እንደማይቀር ተረጋገጠ - ይህንን ነው ከትንሳኤ በዓል የምንማረው።ኢትዮጵያን ሰቅሎ መቅበር፣ ቀብሮም ማስቀረት አይቻልም። የተሰቀለች፣ የተቀበረች የምትመስልበት ጊዜ ግን አለ። በጠላቶቿ የተሸነፈች የምትመስልበት ቀን ግን ነበር፣ አለ። ራቁቷን በጨለማ ውስጥ የቆመች የምትመስልበት ጊዜ ግን ነበር፣ አለ። ወዳጆቿ ሸሽተዋት፣ ልጆቿ ተስፋ ቆርጠውባት፣ አዋቂዎቿ ሟርት ነጋሪዎች ሆነውባት፣ ፀሐይ የጨለመባት፣ጨረቃም ደም የለበሰችባት፣ ኮከቦቿም የረገፉባት

የሚመስልበት ጊዜ ነበር፣ አለ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን ትንሳኤ ይመጣል። የዓርብም ሆነ የቅዳሜ ጉዞ ወደ ትንሳኤ ነው። በግርግር ውስጥ፣ በስሜትና በነውጥ ውስጥ ያለ ሰው፣ አርቆ ለማየት ተስኖት እንጂ ትንሳኤ የሚጀምረው ከዓርብ ነው። ዓርብ ዕለት ብዙ ሰው የሚያየው የሕዝቡን ጩኸት ነው፤ የክርስቶስን መሰቀል ነው፤ የፀሐይን መጨለምና የጨረቃን ደም መልበስ ነው፤ የከዋክብትን መርገፍ ነው። የትንሳኤን ታሪክ ማየት የሚችሉ ጥቂቶች ግን የመጋረጃውን መቀደድ፣ የአለቶችን መሰንጠቅ፣ የመቃብሮችን መከፈት፣ የሙታንንም መነሳት ዓርብ ዕለት ያያሉ። በዓርብ ጨለማ ውስጥ የትንሳኤን ብርሃን ከተሻረችው ሰንበት ጀርባ ይማትራሉ። በታምራት፣ በደም እና በጩኸት ከታረሰው የዓርብ ሰማይ አልፎ፣ ቀቢጸ ተስፋ ከተጣባው የቅዳሜ ጀምበር ወዲያ፣ የተስፈኛው ብርቱ ልብ እሑድ ሌሊት ላይ የሚገለጠውን ትንሳኤን ያያል። ኢትዮጵያችንም እንዲሁ ናት። የተሸነፈችና የደከመች፣ የተሰቀለችና የሞተች፣ ያለቀላትና ያከተመላት በሚመስልበት ጊዜ ውስጥ ትንሳኤ ዋ ከሩቁ ይታያል። በዛሬው ማዕበል የማይወሰዱና፣ በአይሁድ የሀሰት ወሬ የማይናዱ የማይቀር ትንሳኤዋን ያዩታል። አየሩን ክፉ ወሬ ቢሞላውም፤ ከሙታን የተነሱት ግን ወደ ከተሞች ገብተው መልካሙን ወሬ ያወራሉ። ልጆቿ የተከፋፈሉ ሆነው ዓርብን ያሳልፉታል። እንደ ዮሐንስ ያሉት ጸንተው፣ እንደ ጴጥሮስ ያሉት ተጠራጥረው፣ እንደ ይሁዳ ያሉት ክደው፣ ሌሎቹ ደግሞ ፈርተውና ደንግጠው ዓርብን ያሳልፋሉ። ትንሳኤ ሲመጣ ግን የካዱት ይጠፋሉ፤ የተጠራጠሩት ያምናሉ፤ ያመኑት ይጸናሉ፤ የፈሩትም ይደፍራሉ። እንደገናም ተመልሰው ላይበተኑ አንድ ይሆናሉ። በዕለተ ትንሳኤ ሁሉም ይደመራሉ። ድንጋዩም ይነሳል፣ መቃብሩም ይከፈታል፤ ሙሰናም ይቀራል፤ መግነዙም ይፈታል። ትንሳኤው እንዳይኖር ከብበው የሚጠብቁ ይበተናሉ። አለቀ ደቀቀ እያሉ ሲተነትኑ የነበሩ ያፍራሉ። በነፍሳችን ሲወራረዱ የነበሩ ሁሉ ይደነግጣሉ። ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ ተስፋ የላትም ያሉ ሁሉ እነርሱ ራሳቸው የትንሳኤዋ ማስረጃዎች ይሆናሉ። ዓርብ የጀመረው ትንሳኤ እሑድ ይደመደማል። እንደ አይሁድ ለብቻቸው አድመው ዕጣ ፈንታችንን የወሰኑብን ሁሉ ከእውነቱ ጋር ይጋፈጣሉ። ‹በሞት ተፈጸመ፣ በመቃብርም

ተደመደመ› ብለው ታሪካችንን ሊጽፉ የቋመጡ ሁሉ እንደገና ብዕራቸውን ለትንሳኤያችን ያነሳሉ። እኛ የሞት መልዕክተኞች አይደለንም፤ የሕይወት አብሳሪዎች እንጂ። እኛ የመቃብር ጠባቂዎች አይደለንም፤ የትንሳኤ መለከቶች እንጂ። እኛ የጨለማ አበጋዞች አይደለንም፣ የብርሃን መልዕክተኞች እንጂ፤ እኛ ከጨለመች ፀሐይና ደም ከለበሰች ጨረቃ ይልቅ የተተረተረውን መጋረጃ፣ የተከፈቱትን መቃብሮች፣ የተነሱትን ሙታን፣ የተናወጡትን ተራሮች እናያለን። እኛ ከሕማማት በኋላ ፋሲካ፣ ከመከራም በኋላ ደስታ መኖሩን እናምናለን። ለእርሱም እንጋደላለን። የትናንቱን ዛሬ ዘግተን፤ የነገውን ዛሬ እንጀምራለን። ይህቺ ኢትዮጵያ ናት -ዓርብን አሳልፋ፣ ቅዳሜን ድል ነስታ - እንደ ገና የምትነሳ፣ እንደገናም የምታሸንፍ።

ኑ! የመቃብር ጠባቂነታችንን ትተን - የኢትዮጵያን ትንሳኤ እናብሰር

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!

መልካም በዓል!